

**በሰመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ**

# የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳን ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የ2024 ዓመታዊ ሪፖርት

**ማርች 30፤ 2025**

# የይዘት ስንጠረዥ (Table of Contents)

ሀ - የመንፈሳዊ አገለግሎት ዓመታዊ ሪፖርት ገጽ 2

ለ - የሰንበት ትምህርት ቤት ዓመታዊ ሪፖርት ገጽ 3

ሐ - በጽሕፈት ቤት የተከናወኑ እና የተወሰኑ የ2024 ዋና ዋና ጉዳዮች ገጽ 3

መ - የጥገና እና እድሳት ዓመታዊ ሪፖርት ገጽ 4

ሠ - የዕቅድና ልማት (የፋይናንስ) ዓመታዊ ሪፖርት ገጽ 5

# <u>በስመ አብወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ</u>

## የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የ2024 ዓመታዊ ሪፖርት

## *<u>ሀ - የመንፈሳዊ አገለግሎት ዓመታዊ ሪፖርት</u>*

፩) ዘወትር ጠዋት ከሰኞ እስከ ዓርብ የነግህ (የጧት) ጸሎት በቀሲስ ዓለም እሸት ከርዕስ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጋራ በመገናኛ ዘዴ online ደርሷል

፪ - ዘወትር ከሰኞ እስከ ዓርብ የሠርክ (የማታ) ጸሎት ደርሷል

፫ - ዘወትር ቅዳሜ የነግህ (የጧት) ጸሎት ደርሷል

፬ - የሰንበት ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርት ተሰጥቷል

፭ - ከሰዓት በኋላ ለዲይቆናት ትምህርት አስተምረናል

፮ - በቀጠሮ የሚመጡ ምእመናንንም ጸሎትና የምክር አግልግሎት ሰጥተናል

፯ - በማንኛውም ቀንና ሰዓት ለመጡ ምእመናን የጸሎትና የምክር አገልግሎት ተሰጥቶአል

፰ - የታመሙ ሰዎች በአካልና በመገናኛ ዘዴ (በዙም) የጸሎትና የምክር አገልግሎት ተሰጥቶአል

፱ - ዘወትር እሁድ ከሌሊቱ 4:00 am ጀምሮ የሌሊት ጸሎት ፤ ጸሎተ ቅዳሴ ፤ ስብከተ ወንጌል በተለያዩ መምህራን ክርስትና እና ጸሎተ ፍትሐት ተደርጓል

፲ - አዲስ ዓመት (ዕንቁጣጣሽ) የመስቀል በዓል ፤ የልደት በዓል ፤ የጥምቀት በዓልና የትንሣኤን በዓል በልዩ ልዩ ዝግጅት አከብሮአል

<u>፲፩</u> - የታህሣሥ አማኑኤል ፤ የየካቲት ኪዳነ ምሕረት ፤ የግንቦት አማኑኤልና የነሐሴ ኪዳነ ምሕረት በዓለ ንግሥ ከልዩ ልዩ ቦታ በመጡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ፤ ዲያቆናት እና ምእመናን በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል

<u>፲፪</u> - የነነዌን ጾም ምክንያት በማድረግ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሊቀ ጳጳስ ዘአኩስም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ለሀገራችን ለኢትዮጵያና ለቤተ ክርስቲያናችን ምሕላና ጸሎት እንዲደረግ በሰጡት አባታዊ ትእዛዝ መሠረት ምሕላና ጸሎት ለሦስት ቀን በዙም አካሂደናል

## ለ - የሰንበት ትምህርት ቤት ዓመታዊ ሪፖርት

የደብራችን የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ባሳለፍነው 2024 ዓ.ም የአገልግሎት ዘመን የተለያዩ ተግባሮችን አከናውኗል።

፩ - በዕለተ ሰንበት ተገኝተው ያጠኑትን እና ያዘጋጁትን መዝሙሮችን አቅርበዋል።

፪ - በካህናት አባቶች ትዕዛዝ ሲጠየቁ የተለያዩ አገልግሎቶችን እገዛ አድርገዋል።

፫ - በዓመታዊ እና ዓበይት በዓላት ተገኝተው ከዝማሬ በተጨማሪ ከምእመናን ጋር በመተባበር የፅዳትና የተለያዩ አገልግሎቶችን አከናወነዋል።

፬ - ሕፃናቶችን መዝሙር በማስጠናትና በማሰልጠን አስተባብረዋል።

፭- ከቤ/ክ ምእመናን በፈቃደኝነት ተውጣተው ሕፃናትን በማስተማር ከሚያገለግሉ መምህራን ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ሁሉ አገልግሎት አከናውነዋል።

## ሐ - በጽሕፈት ቤት የተከናወኑ እና የተወሰኑ የ2024 ዋና ዋና ጉዳዮች

፩ -ማርች 10 ፤ 2024 ሰበካ ጉባኤ የጠቅላላ ስብሰባ ጠርቶ የ2023 ዓ/ም ሪፖርት አቅርቧል

፪ - የ2024 በጀት ተዘጋጅቶ ለምእመናን ቀርቦ ጸድቋል

፫ - በመተዳድሪያ ደንባችን አንቀጽ 9 መሰረት አክቶበር 27 ፤ 2024 ሰበካ ጉባኤው ጠቅላላ ስብሰብ ጠሮቶ የሰበካ ጉባኤ አባላት ምርጫ አካሂዷል

፬ - በዓላትን በአግባቡ እንድናከብር ሰበካ ጉባኤ አስተባብሯል ፤ በዓላቱም የኪዳነ ምሕረት እና የአማኑኤል በዓለ ንግስ ፤ እና የመስቀል በዓለ ፤ ሲሆኑ በተጨማሪም ዘጠኙንም ዓበይት በዓላትን ፤ ትስብዕት፤ ልደት ፤ ጥምቀት ፤ ደብረ ታቦር ፤ ሆሣዕና ፤ ስቅለት ፤ ትንሣኤ ፤ ዕርገት እና ጰራቅሊጦስ ተከብረዋል

፭ - ሰበካ ጉባኤው ለቤተ ክርስቲያናችን ገንዘብ የማግኛ መንገድ አቀነባብሮ የሚከተሉት ፈንድ ሬዚይንግ ተደርጓል:

- የአዲስ ዓመት በዓል (ዕንቁጣጣሽን) በማክበር ትኬት ተሸጦ ገንዘብ ስብሰባ ተደርጓል
- የኢትዮጵያን ቀን ፕሮግራም ላይ ተሳትፈናል ፤ በፕሮግራሙ ላይ ቁሳቁሶችን በመሸጥ ገንዘብ ተሰብስቧል
- ጊቪንግ ቱዩስዴ በሚባለው የገንዘብ አሰባሰብ ዓመታዊ ፕሮግራም ላይ ተሳትፈን ገንዘብ አግኝተናል

፮ - መተዳደሪያ ደንቡን በመከተል በ2024 አንድ ቤተሰብ አባል አድርገን መዝግበናል

፯ - የቤተ ክርስቲያን አካውንት በአንድ ባንክ ብቻ ይሁን በሚል ተነጋግረን ስምምነት ላይ ደርሰን ውስፍስ ባንክ አከውንት ተከፍቷል ፒኤንሲና ዊልስፋርጎ በቅርቡ ይዘጋሉ።

፰ -በመተዳደሪያ ደንባችን አንቀጽ 25 መሰረት የምግባረ ሠናይ (የበጎ አድራጎት) ኮሚቴ አቋቁሟል

፱ - የተክኖሎጂ ክፍል አቋቋሟል

፲ - ለበዓለ ንግሥ ወይም ክብረ በዓል ለማክበር የመጡ ካህናትን አስተናግዷል

፲፩ - በየወሩ የሚከፈሉትን የአስተዳደር ክፍያዎች በቀጥታ (direct payment) ከባንክ አካውንታችን እንዲከፈል አድርገናል

፲፪ - ለእመናን እና ለገንዘብ ማሰባሰቢያ (fundraising) እንዲመች ዘምናዊ ክሪድት ካርድ ማሽን አስገብተናል

፲፫ - ምእመናን የሚያበረክቱትን ገንዘብ በዓመቱ መጨረሻ ለታክስ እንዲጠቅማቸው ደብዳቤ እዘጋጅቶ ሰጥቷል።

## መ - የጥገና እና እድሳት ዓመታዊ ሪፖርት

ለቤተ ክርስቲያናችን ሕንፃ አስፈላጊውን እድሳትና ጥገና በማድርግ ባሳለፍነው ዓመት የሚከተሉትን ተግባሮች አከናውኗል።

፩ - በማርች 24, 2024 የአፓርትመንቱን በዝናብ ምክንያት ከውጭና በውስጥ የተበላሹትን ጣሪያና ግድግዳ የእድሳትና ጥገና ለማድረግ ለሠራተኛ እና ዕቃ ወጪ ኮንትራት በመስጠት አሰርቷል

፪ - በሜይ 05, 2024 የቤተ መቅደሱ መብራት በአዲስ እንዲቀየር ምእመናኑን በማስተባበር ዕቃውን በonline order ተደርጎ ተሰርቷል

፫- በሜይ 26, 2024 ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተጨማሪ የመብራት ብርሃን በማስፈለጉ  ሁለት ትልልቅ LED florescent ተገዝቶ በሰራተኛ አሰርቷል።

፬ -ጁን 09, 2024 ለቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ሥዕሎችን ለማሠራት የቤተ ክርስቲያናችንን ምእመናን በማስተባበር ከሃገራችን ኢትዮጵያ ተሠርቶ ፍሬሙን እዚሁ በሚያምር መልኩ ተሰርቷል።

፲- በዲሰምበር 15, 2024 የአየር ማሞቂያ (Heater) በነበረው ቀዝቃዛ አየር ምክንያት አልነሳ በማለቱ በሰራተኛ እንዲሰራ ተደርጓል።

፲፩ - በዚህ ዓመት በቤተ ክርስቲያናችን የተሰሩትን ጥገናና እድሳትን በተመለከት የተለያዩ ባለሚያዎችን አወዳድሮ የተሻለ ዋጋና የስራ ልምድ ያለውን በማየት እንዲሰራ ተደርጓል።

## ሠ - <u>የዕቅድና ልማት (የፋይናንስ) ዓመታዊ ሪፖርት</u>

፩ - በ2024 ገንዘብ ማሰባሰብ የተደረገው በአራት (4) መንገዶች በኩል ነው። እነዚህም፦

- በፊላደልፊያና እና አካባቢው በተደረገው የኢትዮጵያ ቀን (Ethiopian's Day)
- የኢትዮጵያን አዲስ አመት በአል አስመልክቶ
- በ Giving Tuesday (ጊቪንግ ቲውስዴይ) እና
- በንዋየ ቅድሳት ሽያጭ

፪ - በ9/7/24 የኢትዮጵያ ቀን አስተባባሪ ኮሚቴ (Ethiopian's Day Planning Committe) ባዘጋጀው በዓል ላይ ቤተ ክርስቲያናችን ተሳትፎ አድርጎ በእለቱ ቀን ከልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ሽያጭ $1,359 ለቤተ ክርስቲያናችን ገቢ ሆኗል።

፫ - በ9/14/24 ለቤተ ክርስቲያናችን ገቢ ማሰባሰቢያ የPicnic ዝግጅት ተደርጓል። እንደምታስታውሱት፣ በሁላችሁም ትብብር ዝግጅታችን በአማረ ሁኔታ ካሰብነው በላይ ውጤታማ ሆኖልናል። በዚህ ዝግጅት $3,119 ለቤተክርስቲያን ገብቷል።

፬ - በአቶ ኤፍሬም ካባ አደራጅነት በGiving Tuesday (ጊቪንግ ቲውስዴይ) የቤተ ክርስቲያናችን የአፓርትመንት ቤዝመንት እድሳት እና በኋላ በኩል ያለውን የመግቢያ በር ድልድይ ለመቀየር በተደረገው ውሳኔ $9,561 ገቢ ተደርጓል።

፭ - የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ለንዋይ ቅድሳት ሽያጭ እንዲቀርብ አበርክተዋል። በ2024 ከነዋይ ቅድሳት ሽያጭ $5,449 ገቢ ሆኗል።

በአጠቃላይ በ 2024 በእቅድና ልማት ክፍል በኩል $19,488 ለቤተ ክርስቲያናችን ገቢ ማድረጉን ሲገልጽ በታላቅ አክብሮት ሲሆን እንዲሁም በቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ስም እግዚአብሄር ይስጥልን በማለት ምስጋና ያቀርባል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት
ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ